# የተሳካ ሕዝባዊ ስብሰባ በኑርንበርግ ከተማ

# ጀርመን

በጀርመን ሀገር በኑርንበርግ ከተማ በሰኔ 15 ቀን 2005 ዓ.ም.(ጁን 22 ቀን 2013) የተካሄደው ሕዝባዊ ስብሰባ በተሳካ ሁናቴ ተጠናቀቀ።

ይህ ሕዝባዊ ስብሰባ የተዘጋጀው በኑርንበርግ አካባቢ በሚንቀሳቀሰው የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ፤ በፓርቲው አባላትና በዞናል ኮሚቴ ትብብር የተዘጋጀ ሲሆን ለተሰብሳቢዎቹ ገለፃ ለመስጠት የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባል የሆኑት ዶ/ር ዘነበ ተሾመና በጀርመን የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ ሊቀመንበር ጓድ ሰለሞን ገብረ መስቀል ተገኝተው ነበር።

የዝግጅቱ ሂደት የተመራው የአካባቢው የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ አባል በሆኑት ወጣት መቅደስ ፋንታሁን ሲሆን በዚሁ ስብሰባ በአካባቢው ከሚገኙ የኦርቶዶክስ ተዋህዶና እንዲሁም የእስልምና እምነት ተከታይ አንስቶ ለሎችም በርካታ የድጋፍ መግለጫዎች ያሰሙ የአካባቢው የሲቪል ድርጅቶችም የተገኙበትም ነበር።

የሕዝባዊ ስብሰባው ዝግጅት ፕሮግራም ቅደም ተከተል በወጣት መቅደስ ፋንታሁን ከተገለፀ በኋላ ጓድ ሰለሞን አጠር ባለ የመግቢያ ንግግራቸው በቅርቡ በኑርንበርግ አካባቢ የሚኖሩ የስደተኛውን ክብርና ማንነት የሚዳፈር አግባብነት የሌለውና አሳፋሪ ቅስቀሳ መካሄዱን በመንቀፍ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች ለመብታቸው በፅናትና በጋራ ቆመው እንዲንቀሳቀሱና ኢሕአፓም በበኩሉ የስደተኛው ፍላጎትና ጥያቄ እንዲሳካ በተቻለው አቅም የሚረዳና ከጎናቸው እንደሚቆምም ገልፀዋል።

ከሳቸው በመቀጠል ወጣት ሳሙኤል ደመረ ኢሕአፓ የጠራውን ሀገር አድን ዘመቻ ይዞት ከገለፁ በኋላ ወጣት ሊያ ዮሴፍ በበኩላቸው የወጣት ሴቶች በትግሉ ተሳትፎ ወሳኝነትን አስመልክቶ አፅንዖት የተሰጠበትና የትግል ጥሪ ያዘለ ንግግር አድርገዋል። ወጣት ሊያ ንግግራቸውን በመቀጠል ወያኔ በኢትዮጵያዊያን ሴቶች ላይ እያደረሰ ያለውን በደልና ጭቆና ለማደብስበስና ትግላቸውንም ለማድበዝበዝ ጥቂት ሴቶችን ለይስሙላ በመድረክ እያሳየ ያለውን ድርጊቱን በማውገዝ የፆታ እኩልነት በተግባር የሚረጋገጠው ሴቶች ለመብታቸው ቆርጠው በመታገል የወያኔን አገዛዝ ከሕዝብ ጫንቃ ላይ አስወግደው ራሳቸው የመብት ባለቤት ሲሆኑ ብቻ መሆኑን ከፍተኛ አፅንዖት በተሞላበት ሁኔታ የመደራጀትና ተደራጅቶም በፅናት የመታገል ጥሪያቸውን ለተሰብሳቢው አሰምተዋል።

የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር አባል የሆኑት ዶ/ር ዘነበ ተሾመ በበኩላቸው ገለፃቸውን የጀመሩት በቅድሚያ ላለፉት 40 አመታት ለመብት መከበርና ለዜጎች ነፃነት መጎናፀፍ፤ ለሀገር ሉአላዊነት መከበር ሲሉ የተሰዉትን የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም የዴሞክራሲያዊ ኃይሎች አባላት በአንድ ደቂቃ የሕሊና ፀሎት እንዲታወሱ በመጠየቅ ነበር። በማስከተለም በበኩላቸው እሳቸው ተናጋሪ ተሰብሳቢው አዳማጭ ሳይሆን በሚያቀርቡላቸው የመወያያ ገለፃዎች ላይ በመንተራስ ከአዳማጩ ጋር በመወያየት የጋራ ግንዛቤ ለማግኘት ትብብር ለመፍጠር እንደሆነ በመጠቆም ለውይይት መንደርደሪያ ይሆን ዘንድ ስለ ሕዝባዊ የጋራ ደህንነትና የግል ጥቅም ውስጣዊ ይዘታቸው ምን እንደሆነ የሚያስረዳ ትንተና ካቀረቡ በኋላ ይህ ግንዛቤ ለኢሕአፓ የፖለቲካ ትግል ዋና መሰረት እንደሆነ አብራርተዋል። በማስከተልም ይኸው የጋራ ደህንነትና ጥቅም ግንዛቤ ከወያኔ አገዛዝ ጋር እሳትና ጭድ የሚያደርጋቸው እንደሆነና የወያኔ ፖለቲካ በቡድን መብት በመሸፈን የግለሰብ ዜጋ ነፃነትን የሚደፈጥጥ በመሆኑ የግዴታ ወደ አምባገነንነት የሚወስድ እንደሆነና ይህም በተግባር መረጋገጡን፤ በአንፃሩ የኢሕአፓ ፖለቲካ እየቀሰቀሰ፡ እያደራጀ" ተደራጅቶም የማታገል ሂደቱ ወደ መድብላዊነት ጠባይ ወዳለው ሥርአትና ዴሞክራሲያዊ አቅጣጫ የሚወስድ እንደሆነ በትንተናቸው በሰፋት አብራርተዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘም ወያኔ የቡድን መብትን በማስቀደምና በልጥጡ በመተርጎም የግለሰብ ዜጋ ነፃነትን እንደሚያፍን፡ ነፃ አውጪ ያለ ሁሉ ለነፃነት መጎናፀፍ ሳይሆን የግለሰብ ዜጋ ነፃነትንና መብትን የሚቃወሙ እንደሆኑ ወያኔና ሌሎች በነጻ አውጪነት ሥም እየተንቀሳቀሱ ያሉትን በምሳሌነት

በመጥቀስ ገልፀዋል። ኢሕአፓ በበኩሉ ለቡድን ጥቅም መሰረቱ ግላዊ ጥቅም እንደሆነ በመጥቀስና በኔ አውቅልሃለሁ አባዜ የሕዝብና የጋራ ጥቅም አስቀድሞ የሚታወቅ ነው በማለት የሚሟገቱና ይህንንም ተግባራዊ የሚያደርጉ አምባገነንት የሚጠናወታቸውና ለማህበራዊ እድገትና ጥንካሬ መሰረታዊ የሆኑትን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን የማያከብሩ እንደሚሆኑ በምሳሌነት የወያኔ አገዛዝን የመሰሉ አገዛዞችን በመጥቀስ አብራርተዋል። የሕዝብ ጥቅም አስቀድሞ ሳይሆን በዴሞክራሲ ውይይት የሚገኝ እንደሆነ ለዚህም መሰረቱ የዜጎች ግላዊ ነፃነታቸውን መጎናፀፍና መሰረታዊ የሆኑት ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ምሶሶ እንደሆነም እንዲሁ በስፋት አብራርተዋል። በመቀጠልም በዚሁ ትንታኔና የሕዝባዊ ጥቅም ግንዛቤ በመነሳት የአንድን አገዛዝ ድርጊቶች ለመመዘን እንደሚቻልና ጭፍን ድጋፍ ሳይሆን ሚዛናዊ የሆነ አመለካከትን ለማግኘት የሚያገለግል እንደሆነም በቅርቡ የአባይን ግድብ በተመለከተ እየቀረቡ የሚገኙት የተለያዩ አስተያየቶች መሰረታቸው ይኸው በኔ አውቅልሃለሁ ባይነት በተጠናወታቸው ክፍሎችና ቅድሚያ በሚመለከታቸው ኃይሎች ዴሞክራሲያዊ ውይይት መደረግን የትግላቸው አካል አድርገው በሚመለከቱ መካከል እንደሆነ ለመገንዘብ እንደማያዳግት በዝርዝር ገልፀዋል።

ለውይይት መንድርደሪያ የቀረቡት አስተያየቶች ከተጠናቀቁ በኋላ ከእረፍት መልስ በቅድሚያ የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ በኖርዌይ ቅርንጫፍ ተወካይ ጓድ ነጋ አበባው(ሚኒሊክ) ስለ ወጣቱ ክንፍ ባጠቃላይ በተለይም በኖርዌይ ስለሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ማብራሪያውን ለተሰብሳቢው ካስደመጠ በኋላ በርካታ ጥያቄዎች ከአዳማጩ ቀርበው ከመድረኩም ለቀረቡት ጥያቄዎች ሰፋ ያለ ገለፃና ማብራሪያዎች በመስጠት የቀኑ ትዕይንት ተሰብሳቢውን ባረካና በተሳካ ሁናቴ ተጠናቋል።

የስብሰባው አዳራሽ በተለያዩ የትግል መፈክሮች *„ወጣቱ የሀገር አለኝታ ነው!“ ፤ „ ከአባይ በፊት አምባገነንነት ይገደብ“* የመሰሉና እንዲሁም በሀገራችን ሰንደቅ አላማ ያሸበረቀ ነበር። ለዚሁ ሕዝባዊ ስብሰባ ተብሎ የተዘጋጀ ልዩ እትም የአደራ መፅሄትና የፓርቲውንና የወጣት ክንፉን የያዘ ካኒቴራ ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን በተለይም ለተሰብሳቢዎቹ የተዘጋጀ ምግብና መጠጥ እንዲሁም ጣዕምን የሚማርክ ትኩስ ቡና በሀገር ባሕል መሰረት ተዘጋጅቶ መቅረቡ በውይይቱ በንቃት ለመሳተፍና መልካም ግንዛቤን ከውይይቱ ለማግኘት እንደረዳ ምንም ጥርጥር የለውም።

የስብሰባው ተካፋዮች በውይይቱ ገለፃ በመርካታቸውና ሂደቱም በተሳካ ሁናቴ መጠናቀቁን ከግምት በማስገባት በስብሰባ ጥሪው እንደተጠቆመው በጀርመን ሀገር ነዋሪ ከሆኑ ኢትዮጵያዊያን ጋር ኢሕአፓ የኃሳብ ልውውጦችና ውይይት ብሎም የትግል አንድነት በበለጠ ለመፍጠር ይቻል ዘንድ መሰል የውይይት መድረኮችና ስብሰባዎች በሌሎች ከተሞች ቢዘጋጁ የበለጠ ጠቃሚ እንደሆነ ስለተጠቆመ ይህ ስኬታማ ይሆን ዘንድ ጥረት እንደሚደረግ የሚመለከታቸው አካላት ቃል ገብተዋል። በመጨረሻም ለመዝናኛ በተዘጋጀው ቦታ በመገኘት ደስታና ናፍቆትን ያዘለ ጭውውት ከተደረገ በኋላ ሁሉም በመሰነባበት የቀኑ የትዕይንት መጋረጃ ተዘግቷል።

ከኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ በጀርመን

24.06.2013


E P R
Annual Meeting in
22 06 2013


22 06 2013


Diskussions- Seminar in Nürnberg
22 06 2013


Diskussions- Seminar in Nürnberg
Meeting in Nürnberg, Germany
22 06 2013


Diskussions- Seminar in Nürnberg
Annual Meeting in Nürnberg, Germany
June 22, 2013
22 06 2013


22 06 2013


22 06 2013


E P R P
Annual Meeting in Nürnberg, Germany
ወጣቱ የሐገር አለኝታነው!!
22 06 2013


22 06 2013


E P R P
Annual Meeting in Nürnberg, Germany June 22, 2013
22 06 2013


ወጣቱ የሐገር አለኝታነው!!
22 06 2013


ሕዝባዊ ስብሰባ በኑርንበርግ
ሰኔ 15 2005 (ኢሕአፓ)
Seminar in Nürnberg
22 June 2013 (EPRP)
June 22, 2013
22 06 2013


22 06 2013


An nu al Me
22 06 2013


22 06 2013


Seminar in Nürnberg
2013 (EPRP)
Nürnberg, Germany
June 22, 2013
22 06 2013